# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

የካቲት 2014 ዓ.ም.


## የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች በጋራ በመሥራት አቅማቸውን በማጠናከር የንግዱን ማኅበረሰብ እንዴት በተሻለ አሠራር እና ስትራቴጂ ማገልገል እንደሚቻል መከሩ





የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች በጋራ በመሥራት አቅማቸውን በማጠናከር የንግዱ ማኅበረሰብን እንዴት በተሻለ አሠራር እና ስትራቴጂ ማገልገል እንደሚቻል መከሩ ።

የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች በግሉ ዘርፍ ዕድገት፣ በንግድ እና ኢንቨስትመንት፣ በገጽታ ግንባታ፣ የማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት እና በአቅም ግንባታ እንዲሁም በምክር ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ፣ በሰራተኞች የርስ- በርስ ግንኙነት፣ በሕንጻ አጠቃቀም እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ ሊያከናዉኗቸው በሚገቡ ጉዳዮች ላይ የካቲት 29/ 2014 ዓ.ም በሰፊው ተወያዩ፡፡

በዚህ የሁለቱ ም/ቤቶች የማኔጅመንት አባላት በተሳተፉበት ገንቢ የውይይት መድረክ ላይ የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ም/ዋና ፀኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ እንደተናገሩት ሁለቱ ምክር ቤቶች በጋራ የሚሰሩ ስራዎችን በፍቅር እና በትብብር መንፈስ ተቀራርበው በመስራት የምክር ቤቶቹን መልካም ስምና ገፅታ መገንባት ይገባቸዋል ብለዋል ፡፡

የተካሄደው የውይይት መድረክም በማኔጅመንቱና በሰራተኛው መካከል ብቻ የሚወሰን ሳይሆን የየምክር ቤቶቹ የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ተቀብለውት ወደ ስራ የሚገባ እንደሆነና በውይይቱ የተካፈሉ አመራሮችም በመግባባት እና በትብብር መንፈስ አብረው ሊሰሩ ይገባል ሲሉ አቶ ውቤ አሳስበዋል ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማሪያም በበኩላቸው በማኔጅመንት አባላት የተጀመረውን መልካም ጅማሮ ለጋራ ዓላማ ጠንክሮ በመስራት ዳር ማድረስ ያስፈልጋል ያሉ ሲሆን ፡፡ አክለውም በሁለቱ ምክር ቤቶች ውስጥ ያለውን እምቅ አቅም በመጠቀም ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብለዋል፡፡

በጋራ በሚሰሩ አስተዳደራዊ፣ ኦፐሬሽናል፣ መልካም ግንኙነት፣ የገፅታ ግንባታ በመሳሰሉት አንኳር ተግባራት ላይ ትኩረት አድርገው የድርጊት መርሀ-ግብር አዘጋጅተው ለማኔጅመንቱ እና ለዳሬክተሮች ቦረድ አባላት የሚያቀርቡ ከሁለቱም ምክር ቤቶች የተውጣጡ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል፡፡

ኮሚቴዎችም በምክር ቤቶቹ መካከል በጋራ ሊሰሩ በሚችሉ አበይት ተግባራትን ፤ቀደም ሲል ከአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት በኩል የቀረበውን አጀንዳ መሰረት በማድረግ እና መጨመር ያለባቸውን የውይይት ሃሳቦች የማካተት፣ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ስራዎችን የመለየት፣ የድርጊት መርኃ ግብር የማዘጋጀት፣ የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ እና ውሳኔ የተሰጠባቸውን ጉዳዮች አፈጻጸም የመከታተል እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነቶች አሉባቸው፡፡

⟐

## ም/ዋና ፀሀፊው የህንድ አምባሳደርን ተቀብለው አነጋገሩ

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በኢትዮጵያ የህንድ አምባሳደር ሮበርት ሺትኪንቶግን የካቲት 18 ቀን 2014 ዓ.ም በጽ/ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ፡፡

አምባሳደር ሮበርት ሺትኪንቶግ ከምክር ቤቱ ጋር በጋራ ሊሰሩ የሚችሉ አበይት ጉዳዮች ዙሪያ ገለጻ ያቀረቡ ሲሆን ፤ በዚህም የህንድ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት(FICCI) በቀጣዩ ሳምንት በሚያዘጋጀው የኢትዮ ሜዲካል ኮንግረስ እና ኤክስፖ መድረክ የምክር ቤቱን እገዛ እና ተሳትፎ ጠይቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸኃፊ አቶ ውቤ መንግስቱ በበኩላቸው ከኢምባሲው ጋር በግሉ ዘርፍ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ዙሪያ በጋራ ለመስራት ፍላጎታቸውን አረጋግጠው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የህንድ የቢዝነስ ፎረምን (IBF) ከምክር ቤቱ ጋር ተቀራርበው በሚሰሩበት ሁኔታ ለመነጋገር እንዲቻል መድረክ እነዲመቻች ጠይቀው ከመግባባት ላይ ደርሰዋል፡፡

አክለውም ምክር ቤቱ ከ ከግንቦት 25 - 29 2014 ዓ.ም "የኢትዮጵያን ይግዙ እና በኢትዮጵያ ኢንቨስት ያድርጉ" በሚል መሪ ርዕስ በሚያዘጋጀው 12ኛው የኢትዮ- ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ የህንድ ኩባንያዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ በኢምባሲው በኩል ጥሪ እና ድጋፍ እንዲደረግ እንዲሁም በኢምባሲ በኩል ተሳትፎ እንዲደረግ ጠይቀዋል፡፡

አያይዘውም ኤምባሲው በአቅምግንባታ እና ስልጠና እንዲሁም በምርምር እና አድቮኬሲ ዙሪያ ከምክር ቤቱ ጋር በትብብር መስራቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል የጠየቁ ሲሆን አምባሳደሩ በበኩላቸው ቀደም ሲል ፕሮግራሞች እንደነበሩ አንስተው በተለይም የፊት ለፊት አቅም ግንባታ እና ስልጠና በኮቪድ 19 ምክንያት ለጊዜው መቆሙን አብራርተው ለወደፊቱ በተጠናከረ መልኩ ሲጀመር በጋራ ለመስራት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እና የህንድ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ኮንፌድሬሽን (FICCI) በጋራ ሊሰሩባቸው በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ለመፈራረም እንዲቻል ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ከመግባባት ላይ ደርሰዋል፡፡

⟐


በኢንዱስትሪ ልማት ላይ የግሉ... 2

ኢትዮጲያ ወደ ጅቡቲ... 2

ከውጭ የሚመጡ የጨርቃ... 2

ከቀረጥና ታክስ ነጻ... 2

ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ... 3

መረጃ ያልሰጡ የባንክ... 3

የባንኮች ብድር አመላለስ... 3

የአምራች ኢንዱትሪዎችን... 4

በኮንቴይነር እጥረት... 4

ሳፋሪ ኮም አገልግሎት... 4

አዋሽ ባንክ የሞባይል... 4

በአኅጉራዊ የንግድ ትስስሮች... 5

አራት የቅመማ ቅመም... 5

በአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጣና...5

ሦስት የውጭ ኩባንያዎች... 5

ብሔራዊ ባንክ የመመሥረቻ... 6

የገልፍ የምግብ ኤክስፖ... 6

የድንጋይ ከሰል ለማምረት...6

# በኢንዱስትሪ ልማት ላይ የግሉ ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የኢትዮጵያን ልማት ሊደግፍ ይገባል ተባለ

በኢንዱስትሪ ልማት ላይ በተለይም የግሉ ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የኢትዮጵያን ልማት መደገፍ እንዳለበት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ግንባታን መርቀው በከፈቱበት መርሃ ግብር ላይ ባስተላለፉት መልእክት የኢንዱስትሪ ዘርፍ በመንግስት ልዩ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ገልጸዋል።

በኢንዱስትሪ ልማት ላይ በተለይም የግሉ ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የኢትዮጵያን ልማት መደገፍ እንደሚኖርበት አስገንዝበዋል።

በተለይ የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ተፈላጊነት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ የግሉ ዘርፍ በስፋት ሊሰማራበት ይገባል ብለዋል።

መንግስት ዘርፉን ለመደገፍ የሚጠበቅበትን ሁሉ ድጋፍ እንደሚያደርግ አረጋግጠው፤ ኢትዮጵያዊያን በመደጋገፍ ለአገር ልማት በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ መላኩ አለበል፤ መንግስት አገር በቀል ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመገንባት በትኩረት እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል

የብርታ ብረት ልማት ለምጣኔ ሃብት ሽግግር ሞተር ሆኖ እንደሚያገለግል ጠቅሰው፤ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለማስቀረትና ለስራ እድል ፈጠራ የጎላ ሚና እንዳለው ገልጸዋል።

በአገር አቀፍ ደረጃ ከ500 በላይ ጥቃቅንና አነስተኛ የብረታ ብረት ፋብሪካዎች መኖራቸውንም ሚኒስትሩ ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት በክልሉ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማስፋፋት በርካታ ስራዎች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

በክልል በሺዎች የሚቆጠሩ ከጥቃቅን እስከ ከፍተኛ ያሉ ፕሮጀክቶች ባለፉት ሦስት ዓመታት ወደ ስራ መግባታቸውን ተናግረዋል።

በዛሬው እለት የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ተመርቆ የተከፈተው የአዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ ቀደም ሲል ሲያመርታቸው ከነበሩ ሚስማርና ቆርቆሮዎች በተጨማሪ ፌሮዎች፣ የተለያዩ ሽቦዎች እና ሌሎች የብረታ ብረት ውጤቶችን ያመርታል።

በአሁኑ ወቅት የፋብሪካው ካፒታል 7 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የደረሰ ሲሆን በ5 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ማስፋፊያ አድርጎ ተጨማሪ የብረታ ብረትና ቱቦላሬ ምርቶችን ማምረት ጀምሯል።

ፋብሪካው በአሁኑ ጊዜ ለ900 ሰዎች ቋሚ የስራ እድል የፈጠረ ሲሆን በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምር ደግሞ ለ3 ሺህ ሰዎች የስራ እድል ይፈጥራል ተብሏል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/profile.php?id=100069332524480

# ከውጭ የሚመጡ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት ለዘርፉ የቅድሚያ ቅድሚያ መሰጠቱ ተገለጸ



ከውጭ የሚመጡ የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት ለዘርፉ በገንዘብ አቅርቦት የቅድሚያ ቅድሚያ መሰጠቱን፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ይህ የተገለጸው የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከአገር መከላከያ ሠራዊት፣ ከፌዴራልና ከክልል ፀጥታ ኃይል የሥራ ኃላፊዎች፣ እንዲሁም ዘርፉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የደንብ ልብስና ተያያዥ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለማምረት፣ አቅም መፍጠር በሚያስችል ፕሮጀክት ላይ ውይይት ባደረገበት ወቅት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ከዚህ ቀደም ከተጀመረው የተማሪዎች ጫማና ቦርሳን በአገር ውስጥ የማምረት ፕሮጀክት ጋር ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን፣ በፀጥታ ኃይሎች የደንብ ልብስ በኩልም ከፍተኛ የገበያ ዕድል በመኖሩ ትኩረት መደረጉን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ገልጸዋል።

በተለይ የፀጥታ ኃይሎች አልባሳትና ጫማዎች የደኅንነት ሥጋት እንዳይኖርባቸው፣ በአገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያስችል እንደሆነም አቶ መላኩ አክለዋል። ካለው አቅም አንፃር ከአገር ውስጥ አልፎ ለጎረቤት አገሮች መላክን ታሳቢ ያደረገ ፕሮጀክት መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት በተጀመረው የተማሪዎች ጫማና ቦርሳን በአገር ውስጥ የመተካት ፕሮጀክት፣ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከ718 ሺሕ በላይ ጥንድ ጫማዎች መቅረቡን ገልጸው፣ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ጫማዎች ደግሞ ለመከላከያ ሠራዊት፣ ለፌዴራል ፖሊስና ለክልል ፖሊሶች ከአገር ውስጥ አምራቾች ቀርበዋል ብለዋል።

የአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የሽያጭ ክፍል ኃላፊ አቶ አብዱራህማን ከማል፣ ዘርፉ ከፍተኛ ካፒታልና የሥራ ማስኬጃ የሚፈልግ በመሆኑ በተለይ የገንዘብ አቅርቦት ከፍተኛ ችግር እንደሆነ ገልጸዋል። ዘርፉ ካለው አቅም አንፃር ዕድገቱ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመው፣ በተለይ መንግሥት የገበያ ትስስርን በመፍጠር ድጋፍ ሊያደርር ይገባል ብለዋል።

ፋብሪካዎች በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ከአቅማቸው በታች እያመረቱ የሚገኙት በውጭ ምንዛሪ እጥረትና በብድር አቅርቦት ችግር መሆኑን ገልጸው፣ በተለይ የኢትዮጵያ ልማት ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ትኩረት ሰጥተው ለመሥራት መስማማታቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ አምራቾች ማኅበር የቦርድ አባልና የዕድገት ጋርመንት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ብርሃኑ ደገፉ ደግሞ ለአምራቾቹ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞቹ ከውጭ ከሚመጡ ኢንቨስተሮች ያነሰ በመሆኑ፣ ተወዳዳሪ መሆን አለመቻሉን ይገልጻሉ። የምርቶቹ የጥራት ችግር በጥሬ ዕቃ እጥረት የሚከሰት በመሆኑ የገንዘብ አቅርቦቱን በማሻሻል፣ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ተወዳዳሪ የሆነ ምርት እንዲመረት ድጋፍ ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

ዘርፉ ከአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች አገር ድርጅቶች ጋር የሚወዳደር ስለሆነ የተለየ ድጋፍ ሊደረግ እንደሚገባ ገልጸው፣ ለዚህም ካለው ውስን ሀብት ላይ የቅድሚያ ቅድሚያ እንዲሰጠው ፕሮጀክቱ እንደሚያግዝ አስረድተዋል።

በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን የጥራት ችግር በተለይ በጨርቃ ጨርቅ በኩል በቀለም፣ በጨርቅ ዓይነትና በመሰል የጥሬ ዕቃ ችግሮች፣ እንዲሁም በጫማ ላይ ደግሞ በሶልና በማስቲሽ ጥራት ችግሮች የሚከሰት በመሆኑ ፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥቶ ይሠራል ብለዋል።

በአጠቃላይ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፉ በዓመት ወደ ውጭ የሚላከው ምርት በአማካይ 114 ሚሊዮን ዶላር መሆኑን፣ ከውጭ የሚመጣው ዓመታዊ አማካይ ምርት ደግሞ 545 ሚሊዮን ዶላር መሆኑን አቶ መላኩ ጠቁመዋል። በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ከ1,700 በላይ ጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ፣ እንዲሁም ከ200 በላይ ከፍተኛ የጨርቃ ጨርቅ አምራች ኢንዱስትሪዎች ቢኖሩም፣ በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ ባለመሆናቸው በገቢና በወጪ ምርት መካከል ልዩነቱ ከፍ ማለቱን ገልጸዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24710

# ኢትዮጲያ ወደ ጅቡቲ አትክልትና ፍራፍሬ መላክ የሚያስችላትን ሒደት መጀመሯ ተሰማ

የኢትዮጵያ አበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ አምራቾችና ላኪዎች ማህበር በጅቡቲ ያለውን የአትክልት እና ፍራፍሬ ገበያ በተመለከተ የገበያ ቅኝት አድርጓል ፡፡ የማህበሩ ዳይሬክትር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ ለኢትዮ የንግድ እና ኢንቨስትመንት መድረክ እንደተናገሩት ኢትዮጲያ ወደ አውሮፓ እና አሜሪካ ጥራት ያላቸውን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እየላከች የውጭ ምንዛሬ እያገኘች ነው፡፡ ነገር ግን በቅርበትም ሆነ በአትራፊነት ተመራጭ የሆነውን የጅቡቲ ገበያ እንዳልተጠቀመችበት አንስተዋል፡፡

በተለያዩ መንገዶች የኢትዮጲያ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶች ወደ ጅቡቲ የሚገቡ ቢሆንም ጥራታቸው ተጠብቆ በትላልቅ የገበያ ማእከላት እንዳልገቡ አንሰተዋል፡፡ በጅቡቲ የሚኖሩ የሌሎች ሀገራት ዜጎች ከአውስትራሊያ ከኬኒያ እና ከግብጽ የሚገቡ ፍራፍሬዎችን በውድ ዋጋ እየገዙ መሆኑን በማህበሩ የገበያ ቅኝት ወቅት መመልከታቸውን አቶ ቴዎድሮስ አንስተዋል፡፡

1 ኪ.ግ የኬንያ አቮካዶ በ7 ዶላር በሱፐርማርኬቶች እየተሸጠ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ የኢትዮጲያ አምራቾች እድሉን ለመጠቀም በሚችሉበት ጉዳዮች ላይ ከጅቡቲ አስመጪዎች እና ከሀገሪቱ የቱሪዝም እና ንግድ መ/ቤቶች ጋር መምከራቸውን ተናግረዋል፡፡

በጉዳዩ ላይ በሚቀጥሉት ሳምንታት ተከታታይ ውይይቶች ተደርገው መግባባት ላይ እንደሚደረስም ገልጸዋል፡፡ በሳምንት 2000 ቶን አትክልትና ፍራፍሬ ከኢትዮጲያ ማስገባት የሚቻልበት እድል መኖሩን ከጅቡቲ አትክልትና ፍራፍሬ አስመጪዎች ለማህበሩ መግለጻቸውን አቶ ቴዎድሮስ ተናግረዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/photo/?fbid=127779869767181&set=a.116037684274733

# ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን ለመከታታል የሚያስችል ረቂቅ የትግበራ ማኑዋል ተዘጋጀ



የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችን ለመከታታል ባዘጋጀው ረቂቅ የትግበራ ማኑዋል ግብዓት ለማሰባሰብ ከአስመጪዎችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር አድርጓል፡፡

የትግበራ ማኑዋሉ ዓላማ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ የሚገቡ መሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች ላይ የሚፈጠሩ የተዛባ የንግድ ግብይት ሂደት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የሌለው የዋጋ ጭማሪ የሚያደርጉ ህገ ወጥ ዳላሎች ላይ እርምጃ በመውሰድና የንግድ ግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠርና መሰረታዊ ፍጆታ እቃዎች አቅርቦትን በመጨመር የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋትና ሸማቹን ማህብረሰብ ፍትሃዊ የመሰረታዊ ሸቀጥ ምርትና አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የንግድ አሰራርና ላይሰንሲንግ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ሐሰን ሙሀመድ እንደገለጹት መንግስት በቀጥታ የውጭ ምንዛሬ በመመደብ የመሠረታዊ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እያቀረበ ሲሆን በተጨማሪም ለምግብ ፍጆታ የሚውሉ ስንዴ፣የምግብ ዘይት፣ስኳር፣መኮሮኒና ፓስታና የመሳሰሉ ሸቀጦችን ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ እያደረገ ይገኛል፡፡ እነዚህ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋና በፍትሃዊነት ለህብረተሰቡ እንድቀርቡ ለማድረግ መንግስት ከ18ቢሊዮን ብር በላይ ታክስ እያጣ መሆኑን ገልፀው ተግባሩ በአሰራር ስርዓት ያልተደገፈ በመሆኑ በሚፈለገው ልክ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እየሆነ አይደለም ብለዋል፡፡

በቀጣይ መንግስት ህብረተሰቡን ከኑሮ ውድነት ለመታደግ ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የፈቀዳቸውን የመሠረታዊ ሸቀጦች አካታች በሆነ መልኩ በተመጣጣኝ ዋጋና በፍትሃዊነት ለህብረተሰቡ ይደርስ ዘንድ የአሰራር ማኑዋል በመዘርጋት ስራው በስርዓት እንዲመራ ከሚመለከታቸው አስመጪዎች ጋር ግንዛቤ በመፍጠርና ወደ ትግበራ ለመግባት አስፈላጊ ዝግጅት እያደረገ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው ገልፀዋል፡፡

ምርት ከቀረጥ እና ታክስ ነፃ የምታስገቡ አስመጪዎች ከምንግዜም በላይ ህዝባችንን በታማኝነት የምናገለግልበት ወቅት መሆኑን በመገንዘብ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ የሚናደርግበትን መንገድ ታሳቢ በማድረግና እርስ በርስ ተደጋግፎ ይህን አስቸጋሪ ጊዜ ማለፍ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/photo/?fbid=128325876379247&set=pcb.128326033045898

## ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ የባንክ ስርዓት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ነው



ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ የባንክ ስርዓት በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ እየሰራን ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ ተናገሩ፡፡

ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር ቆይታ ያደረጉት አቶ አቤ ሳኖ፥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሻሻያዎችን በማድረግ የተሻለ የባንኪንግ ሲስተም ተግባራዊ በማድረግ በሀገር ውስጥ ቀዳሚ ባንክ መሆን መቻሉን ተናግረዋል፡፡

የባንኩ ሪፎርም አንድ አካል የሆነው የዋና መስሪያ ቤት ህንፃ መመረቁን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፥ በአዲስ አበባ እና በክልል የቅርንጫፍ ህንፃዎችን ለመግንባት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የተመረቀው የዋና መስሪያ ቤት ዘመናዊ ህንፃም ሁሉንም የባንክ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ እንዲሰጡ በማድረግ ለደንበኞች፣ ለባንኩ ሠራተኞች እና አመራሮች ለሚያከናውኑት ስራ ሚናው ከፍተኛ ነው ብለዋል፡፡

በተለይም በተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የባንኩ ቅርንጫፎችን ክትትል ለማድረግ አስቸጋሪ እንደነበር ገልፀው፥ በተመረቀው ዋና መስሪያ ቤት ችግሩ እንደሚቀረፍ ተናግረዋል፡፡

ከብድር አሰጣጥ እና አመላለስ ጋር ተግዳሮቶች እንደነበሩ የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፥ የወጣቶችን የፈጠራ ሀሳብ ለመደገፍ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራም ነው ያሳወቁት፡፡

እስካሁን ዜጎች ብድር ለማግኘት ንብረት ማስያዝ ይጠበቅባቸዉ እንደነበር አስታውሰው፥ ዜጎች የሚያሲይዙት ንብረት ታይቶ ሳይሆን ያላቸውን የፈጠራ ሀሳብ ለመድገፍ ብድር እንደሚመቻች ይደረጋል ብለዋል የባንኩ ፕሬዚዳንት፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ዓለም-የደረሰበትን-ዘመናዊ-የባንክ-ስርዓ/

## መረጃ ያልሰጡ የባንክ ደንበኞች አካውንቶች እንዳይንቀሳቀሱ ታገደ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ መሠረት እንደ አዲስ መሰጠት ያለባቸውን መረጃዎች ያልሰጡ ባንኮች አካውንታቸው እንዳይንቀሳቀስ መታገዱ ታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ ባንኮች ደንበኞቻቸውን ማንነት እንዲያውቁ አዲስ ባወጣው መመርያ መሠረት ደንበኞቻቸውን መረጃ አሰባስበው መጨረስ አለባቸው የተባለው የካቲት 20 ቀን 2014 ዓ.ም. በመጠናቀቁ እስከ እዚህ ቀነ ገደብ ድረስ መረጃዎቻቸውን ማሟላት ያልቻሉ የባንክ ደንበኞች ተለይተው አካውንቶቻቸው እንዳይንቀሳቀሱ አድርገዋል፡፡

አካውንታቸው እንዳይንቀሳቀስ የተደረጉ ደንበኞች ቁጥር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሲሆን፣ አንዳንዶች ቀነ ገደቡ ከተጠናቀቀ በኋላ ገንዘብ ለማንቀሳቀስ ወደ ባንኮች ቢሄዱም አካውንታቸውን ማንቀሳቀስ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡

አንዳንድ የባንክ ደንበኞች የተጠቀሰውን መረጃ ለማሟላት በተለይ የቀበሌ መታወቂያና ሌሎች መረጃዎች እየተጠየቁ በመሆኑ የታደሰ መታወቂያ የሌላቸው አዲስ መታወቂያ ለማውጣት ወደሚኖሩበት ቀበሌ መሄድ ግድ እያላቸው ነው፡፡ የቀበሌ መታወቂያ ዕድሳት የተጀመረው በተጠናቀቀው ሳምንት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የመታወቂያ ዕድሳት ጥያቄ ያቀረቡ ነዋሪዎች ቁጥር ከፍተኛ በመሆኑ በፍጥነት ማስተናገድ እንዳልተቻለና ይህም የባንክ ደንበኞች መረጃዎቻቸውን አሟልተው አካውንታቸውን እንዳያንቀሳቅሱ ምክንያት እንደሆነ ያነጋገርናቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል፡፡

ከአንዳንድ ባንኮች ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው በተጠቀሰው ጊዜ መረጃ ያልሰጡ ከየካቲት 2014 ዓ.ም. በኋላ አካውንታቸው የታገደባቸው ደንበኞች ተገቢውን መረጃ ለባንኮች ከሰጡ ወዲያው አካውንታቸው እንዲከፈትላቸው እየተደረገ ነው፡፡

ነገር ግን የሚፈለገውን መረጃ ማሟላት ካልቻሉ የባንክ አካውንታቸው ሳይንቀሳቀስ የሚቆይ ይሆናል፡፡

ደንበኞች መረጃዎቻቸውን እንዲሰጡ ከስድስት ወራቶች በላይ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች የተጠየቁ ቢሆንም ጥቂት የማይባሉት መረጃውን ሳያሟሉ በመቅረታቸው ባንኮች የእነዚህን ደንበኞች አካውንት እንቅስቃሴ በማገድ በተለየ ቋጥ እንዲቀመጥ ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የባንክ ደንበኞች በተሰጠው የጊዜ ገደብ አለመጠቀማቸው ለመጉላላት ያደረጋቸው ሲሆን፣ የተጠየቀውን መረጃ ካሟሉ ግን አካውንታቸው ወዲያውኑ የሚንቀሳቀስላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

አብዛኞቹ የባንክ ደንበኞች የሚጠበቅባቸውን መረጃ አሟልተው የሰጡ ቢሆንም በአንዳንድ አካውንቶች ላይ ግን ተጨማሪ የማጣራት ሥራ ሊኖር እንደሚችል ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24881

## የባንኮች ብድር አመላለስ ተግዳሮትና የባንኮች የሐራጅ ጨረታ

በኢትዮጵያ ያሉ ባንኮች ከብድር አመላለስ ጋር ተያይዞ ታይቶባቸዋል በተባለው ክፍተት ዙሪያ ብሔራዊ ባንክ ከባንኮች ጋር እየመረከ ሲሆን፣ ባንኮቹ በበኩላቸው በአንድ ወር ውስጥ ብቻ የጨረታ መነሻ ዋጋቸው ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ የሆኑ ንብረቶችን በጨረታና በድርድር ለመሸጥ ጨረታ ማውጣታቸው ተመለከተ፡፡

ባንኮቹ ለብድር ዋስትና የተያዙ እነዚህን ንብረቶች ለጨረታ ያቀረቡት፣ ያበደሩት ብድር ወቅቱን ጠብቆ ሊመለስላቸው ባለመቻሉ የሰጡትን ብድር ለማስመለስ ነው፡፡ የመጨረሻ ዕርምጃ ነው የተባለውን ለብድር ማስያዣነት የተመዘገቡ ንብረቶችን የመሸጥ አሳሳቢነትም ተንተርሶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከባንኮች ጋር እየተነጋገረ ነው ተብሏል፡፡

ከብድር አመላለስ ጋር በተያያዘ ያነጋገርናቸው የባንክ የሥራ ኃላፊዎች፣ ባንኮች በሕግ በተሰጣቸው መብት መሠረት የሰጡት ብድር ካልተመለሰ፣ ለብድር ዋስትና ወይም ማስያዣነት የያዙትን ንብረት ተረክበው በጨረታ ሸጠው ገንዘባቸውን ማስመለስ የተለመደ ነው ይላሉ፡፡

ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባንኮች ከብድር አመላለስ ጋር እየታየባቸው ያለው ክፍተት እየሰፋ በመምጣቱ የተለያዩ ድጋፍ ተደርጎላቸው ብድሩን ያልመለሱ ተበዳሪዎችን ንብረት ወደ መሸጥ እየገቡ ነው፡፡ ከቅርብ ወራት ወዲህ ቁጥሩ ከፍ ብሎ የታየው የባንኮች ጨረታዎች ባንኮቹ ያበደሩትን ብድር ለማስለስ የመጨረሻ አማራጭ የተባለውን ዕርምጃ ወደ መውሰድ መግባታቸውን ያመለክታል ተብሏል፡፡

ባለፈው አንድ ወር ብቻ በጨረታና በድርድር ለመሸጥ ባንኮች ጨረታ ካወጧቸው ንብረቶች መካከል ትልልቅ ፋብሪካዎች፣ ሆቴሎች፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ሕንፃዎች፣ ሰፋፊ የእርሻ ድርጅቶች፣ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃዎችና ሌሎችን ባንኮች በማስያዣነት የተረከቧቸው ንብረቶች ይገኙባቸዋል፡፡ በእነዚህ ጨረታዎች በከፍተኛ ዋጋ በሐራጅና በድርድር ለሽያጭ ከቀረቡት ውስጥ ወደ አምስት የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች ይገኙባቸዋል፡፡

በተለይ መንግሥታዊ የሆኑት የኢትዮጵያ ልማት ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በጨረታ ለመሸጥ ይፋ ካደረጓዋቸው ንብረቶች ውስጥ ትልልቅ ፋብሪካዎችና ሰፋፊ የእርሻ ኩባንያዎች ይገኙባቸዋል፡፡

የጨረታ መነሻቸው በመቶ ሺዎች ብር ከሚገመቱ ንብረቶች አንስቶ፣ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ የጨረታ መነሻ ዋጋ በሽያጭ የቀረቡ እነዚህ ንብረቶች በሦስት ወራት ውስጥ ይሸጣሉ ተብለው ቀነ ቀጠሮ የተያዘላቸው ናቸው፡፡

ከባንኮች የሚፈለግባቸውን ብድር በወቅቱ ባለመከፈል ለጨረታ ከቀረቡት ትልልቅ ድርጅቶች መካከል የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በ1.13 ቢሊዮን ብር የጨረታ መነሻ ዋጋ ለሽያጭ ያቀረበው ኢቱር ቴክስታይል ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አንዱ ነው፡፡ ኢቱር ቴክስታይል በአንድ ወር ውስጥ ባንክ ይሸጣሉ ከተባሉት ንብረቶች ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሲሆን፣ ይህ ፋብሪካ በተያያዥነት ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ተጓዳኝ ንብረቶችን ጨምሮ የሚሸጥ ሲሆን፣ ፋብሪካው ያለበት ቦታ 100 ሺሕ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ባንኩ ይህንን ፋብሪካ በድርድር ጨረታ የሚሸጠው መሆኑንም አስታውቋል፡፡

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በዚህ ወር ውስጥ ባወጣው ጨረታ ሰለንደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን በ548.14 ሚሊዮን ብር መነሻ ዋጋ በድርድር የሚሸጥ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በዚህ ወር ከወጡ ጨረታዎች ውስጥ በከፍተኛ የጨረታ ዋጋ ለሽያጭ በመቅረብ የጋርመንትና የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ጎልተው ታይተዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከእነዚህ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ሌላ ቢኤም ኢትዮጵያ ጋርመንትና ጨርቃ ጨርቅንም በ277.7 ሚሊዮን ብር የጨረታ መነሻ ዋጋ በሐራጅ ለመሸጥ ጨረታ አውጥቷል፡፡ ኢትዮ ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካንና ተጨማሪ ሁለት መኖሪያ ቤቶችን ከ138 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ መነሻ ዋጋ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በ1.13 ቢሊዮን ብር የጨረታ መነሻ ዋጋ ለሽያጭ ያቀረበው ኢቱር ቴክስታይል ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

በተመሳሳይም 787.5 ሚሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሌላ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካንም ለመሸጥ ያወጣው ጨረታም ከአንድ ወር በኋላ እንደሚከፈት ታውቋል፡፡

ከሰሞኑ ለጨረታ ከቀረቡ ንብረቶች መካከል የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሦስት ትልልቅ የእርሻ ድርጅቶችን በ24.9 ሚሊዮን ብር፣ በ102.7 ሚሊዮን ብር፣ በ36.8 ሚሊዮን ብር የጨረታ መነሻ ዋጋ ለመሸጥ ያወጣው ተጠቃሽ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም ባለፈው አንድ ወር ውስጥ የጨረታ መነሻ ዋጋቸው ከአሥር ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ከ16 በላይ ንብረቶችን ለመሸጥ ተዘጋጅቷል፡፡

የግል ባንኮችም የጨረታ መነሻ ዋጋቸው እስከ 56 ሚሊዮን ብር የሚደርሱ በርካታ ንብረቶችን ለመሸጥ ጨረታ እያወጡ ነው፡፡

ከእነዚህ ጨረታ ማስታወቂያዎች መገንዘብ የሚቻለው፣ በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ብድር ለመመለስ ባለመቻላቸው ያስያዟቸው ንብረቶች ይሸጥባቸዋል የተባሉ ትልልቅና ታዋቂ ኩባንያዎች መኖራቸውን ነው፡፡

ከእነዚህም መካከል በተደጋጋሚ ከተለያዩ ባንኮች ብድር በመውሰድ፣ ብድሩ ባለመመለሱ በርካታ ለብድር ማስያዣነት የተመዘገቡ ንብረቶች የተሸጡበት ተክለ ብርሃን አምባዬ ኮንስትራክሽን አንዱ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም የዋና መሥሪያ ቤቱ ሕንፃን ጨምሮ ለብድር ማስያዣነት ተይዘው የነበሩ ኤድናሞል ሕንፃና ሌሎች ሕንፃዎች በጨረታ የተሸጡ ሲሆን፣ ባለፈው አንድ ወርም ወደ ስምንት የሚሆኑ ንብረቶች ለጨረታ ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ንብረቶች እንደ ሕንፃዎቹ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ባይሆኑም፣ ለብድር ማስያዣነት የተመዘገቡ በመሆኑ በሕጉ መሠረት ለጨረታ የቀረቡ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ የማነ ግርማይ ጠቅላላ የሥራ ተቋራጭ፣ ሲትማክስ ኮንስትራክሽንና ማርያም ተረፈ ኮንስትራክሽን ሰርቪስ የተባሉ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ጨረታ ወጥቶባቸው በከርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ስም የተወሰደ ብድር ባለመመለሱ ለኢንዱስትሪ የሚሆን ይዞታን አዋሽ ባንክ በጨረታ መነሻ ዋጋው 105.8 ሚሊዮን ብር በጨረታ የሚሸጥ መሆኑን አስታውቋል፡፡

በጥራት ኢንተርናሽናል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር አዲስ አበባ ቆዳ አክሲዮን ማኅበር (በመነሻ ዋጋ 112.8 ሚሊዮን ብር)፣ ቀርሺ አነስተኛ የማክሮ ፋይናንስ ባርነባ ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር (53.7 ሚሊዮን ብር) እና ኦኒክ ኢንዱስትሪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር የሚባሉ ኩባንያዎችም ባለፈው አንድ ወር ለወሰዷቸው ብድሮች ማስያዣነት ያስመዘገቡት ንብረት እንደሚሸጥባቸው ታውቋል፡፡

ከባንኮች ንብረት በጨረታ ከመሸጥ ጋር ተያይዞ ያነጋገርናቸው የአንዳንድ ባንኮች የሥራ ኃላፊዎች እንደሚገልጹት፣ ባንኮች ለብድር ማስያዣነት የተመዘገበውን ንብረት ለሽያጭ የሚያቀርቡት አማራጭ በማጣት ነው፡፡ ንብረትን መሸጥ የመጨረሻው አማራጭ መሆኑንም ይጠቅሳሉ፡፡ ባንኮች ያልተከፈላቸውን ብድር ለማስመለስ ይህንን የመጨረሻ አማራጭ ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት ግን ደንበኞቻቸው እስከ መጨረሻው ብድሩን እንዲመልሱ ተጨማሪ ብድር በመስጠት ጭምር የሚደግፏቸው መሆኑን የሚጠቅሱት እነዚሁ የባንክ ኃላፊዎች፣ ተደጋጋሚ የብድር ማራዘሚያ የተሰጣቸው ጭምር ይገኙበታል ይላሉ፡፡ ባንኮቹ ይህንን ሁሉ ካደረጉ በኋላ ብድሩ የማይመለስ ከሆነ ግድ ነውና በሕጉ መሠረት ንብረቱን በመሸጥ ባንኩ ብድሩን ለማስመለስ ይገደዳል ብለዋል፡፡

በተለይ ካለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወዲህ ባንኮች የሰጡትን ብድር ከማስመለስ አኳያ የተለያዩ ተግዳሮቶች ሲያጋጥሙ እንደነበር የሚገልጹት አስተያየት ሰጪዎች፣ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኋላ የተለያዩ ቢዝነሶች በመንግሥት ተጠያቂነት በባንኮቹ ፈቃድ፣ የብድር ማራሚያዎችና

(ወደ ገፅ 4 የዞረ)

# የአምራች ኢንዱትሪዎችን ምርታማነት 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል



በ2014 በጀት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት ከ26 በመቶ ወደ 60 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡

የአምራች ኢንዱትሪው ዘርፍ ግብርና መር የሆነውን የሀገራችን ኢኮኖሚ በመረከብ ብዙ እርምጃዎችን ወደፊት እንዲያሻግር ተስፋ የተጣለበት ነው፡፡ መንግስትም ይህንን እውን ለማድረግ የኢንዱስትሪ ስትራቴጅዎችን በመንደፍ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጅ ዘርፉ የሚፈለገውን ውጤት እያስገኘ አይደለም፡፡ በውጪ ምንዛሪ ግኝት፣ የገቢ ምርቶችን በመተካት፣ በስራ አድል ፈጠራነእና በማምረት አቅም እያስመዘገበ ያለው አፈፃጸም አናሳ ከመሆኑም በተጨማሪ አንዳንድ ፋብሪካዎች ማምረት አቁመው ተዘግተዋል፡፡

ለዚህም ችግር መንስኤ ከሆኑ ጉዳዮች ውስጥ የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ጉድለት፣ የባለድርሻ አካላት የቅንጅት፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት ይጠቀሳሉ፡፡ ደካማ የኢንዱስትሪዎች ትስስር፣ ዝቅተኛ የሰው ኃይል ምርታማነት እንዲሁም የግብይት፣ የኮንትሮባንድና የጸጥታ ችግርም የኢንዱትሪው ምርታማነት እንዲቀንስ ያደረጉት ችግሮች ናቸው፡፡ የባለሀብቱ ያልተገባ ጥቅም ፈላጊነት፣ አካባቢ ተኮር ጸረ-ልማታዊ አስተሳሰብ፣ ዘረፋና ውድመትም የዘርፉ ፈተናዎች ሆነው ቆይተዋል፡፡

እነዚህን ችግሮች በመፍታት የኢንዱትሪዎችን ምርትና ምርታመነት ለማሳደግ የኢንዱትሪ ሚኒስቴር “ኢትዮጵያ ታምርት” በሚል መሪ ሀሳብ የንቅናቄ እቅድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር ገብቷል፡፡ የንቅናቄ እቅዱ ከዚህ ቀደም በተለመደው መልኩ የአንድ ሰሞን ዘመቻ ሳይሆን ከ10 ዓመት የልማት እቅዱ ጋር ተሳስሮ ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ ለረጅም ዓመታት ያለአንዳች መቀዛቀዝ የሚተገበር ነው፡፡ በዚህ እቅድም በተያው በጀት ዓመት የኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት 60 በመቶ ለማድረስ መታቀዱን በኢንዱትሪ ሚኒስቴር የግብይትና መሰረተ-ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሺሰማ ገ/ስላሴ ተናግረዋል፡፡ ከዚህ በፊት በተለያዩ ጊዜያት የንቅናቄ እቅድ ታቅደው መክሸፋቸውን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው የአሁኑ እንደሀገር ሁሉም አመራርና ባለድርሻ መደበኛ ስራው አድርጎ በእለት ከዕለት ክትትል እንደሚመራና በ10 ዓመት፣ በ5 ዓመት እንዲሁም በአንድ ዓመት የሚሰረውን ለይቶ በማቀደ ወደ ተግባር መገባቱን የገለጹት የድሬዳዋ ከተማ ንግድ ኢንዱስትሪና ኢንቨስተመንት ቢሮ ባዘጋጀው የንቅናቄው ማስጀመሪያ መድረክ ላይ ተገኝተው ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የኢንዱትሪዎች አማካኝ ምርታማነት ከ26-46 በመቶ ሲሆን ከዚህ የባሰ ችግር ላይ እንዳይወድቁ ከውይይት ያለፈ ተግባር መፈጸም አለብን ያሉት አቶ ሺሰማ ለንቅናቄ እቅዱ ስኬታማነት አስር ፕሮጀክቶች ተለይተው ለትግበራ በቀዳሚነት መቀመጣቸውንም ጠቅሰዋል

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.facebook.com/photo/?fbid=257344689919947&set=pcb.257344789919937

# በኮንቴይነር እጥረት ዕቃዎችን በወቅቱ ማስጫን ያልቻሉ ኢንዱስትሪዎች ብድር እንዲራዘም ብሔራዊ ባንክ አዘዘ

በኮንቴይነር እጥረትና ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ዕቃዎች በወቅቱ ሊጫንላቸው ላልቻሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ባንኮች ያለ ተጨማሪ ክፍያ ብድራቸውን እንዲያራዝሙላቸው ብሔራዊ ባንክ ማዘዙ ታወቀ፡፡

ብሔራዊ ባንክ የካቲት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. ለባንኮች በጻፈው ደብዳቤ፣ ከጭነት አገልግሎት ጋር ተያይዞ በገጠማቸው እክል ዕቃቸውን በተፈለገው ጊዜ ማስጫን ላልቻሉ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ለተሰማሩ ደንበኞቻቸው የብድር ማራዘሚያ ያለ ተጨማሪ ክፍያ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ማስተላለፉን የሪፖርተር ምንጮች ገልጸዋል፡፡

የብድር ጊዜ ማራዘሚያው እስከ መቼ እንዲሚሆን ደብዳቤው የማይገለጽ ከመሆኑም በላይ፣ ብሔራዊ ባንክ እንዲህ ያለውን ማሳሰቢያ መስጠት ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ እንዳስነሳ ምንጮች ጨምረው ገልጸዋል፡፡ ባንኮች ይህንኑ ጥያቄ ይዘው ለብሔራዊ ባንክ አቤት ይላሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ምንጮች ጠቁመዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ውሳኔዎች ባንኮች ሊያገኙ የሚችሉትን ገቢ እያሳሳ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ከዚህም ቀደም በተመሳሳይ ብሔራዊ ባንክ ለአስመጪዎች ያለ ክፍያ እንዲራዘምላቸው የጠየቀውን ጥያቄ እስካለፈው ወር ድረስ ሲያስተናግዱ የነበረ ሲሆን፣ አሁን በድጋሚ ይህንን ዓይነቱን ማሳሰቢያ መስጠቱ በባንኮች ዘንድ ቅሬታ እንደፈጠረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24861

# የባንኮች ብድር...(ከገፅ 3 የዞረ)

ማራሚያዎችና በተለያዩ ቢዝነሶች ደግሞ የወለድ ቅናሽና ማራዘሚያ ሲያደርግላቸውና ያለተጨማሪ ወለድ ሲያስተናገዱ መቆየታቸውንም አመልክተዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ዕርምጃዎችም ወደፊት ባንኮች ከብድር አመላለስ ጋር ተያይዞ ተግዳሮት እንዲገጥማቸው ያደርጋል ተብሎ ተሠግቷል፡፡

በ2014 የሒሳብ ዓመት ግን ብዙ ባንኮች ካበደሩት ሊሰበስቡት ያቀዱትን ያህል ለማስመለስ አለመቻላቸው ባንኮቹን ሊፈትን ስለሚችል ወደ መጨረሻው አማራጭ መግባታቸው የሚጠበቅ መሆኑንም ያመለክታሉ፡፡

በቅርቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገዥ ይናገር ደሴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በአሁኑ ወቅት ባንኮች የሰጡትን ብድር ከማስመለስ አኳያ ክፍተት ታይቷል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ባንኮች ዕርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

እንደ ባንክ ባለሙያዎች ገለጻ የተሰጠን ብድር ወቅቱን ጠብቆ አለመመለስ ለባንኮች አስቸጋሪ ነው ያሉ ሲሆን፣ በተለይ ባንኮች የሚያበድሩት ገንዘብ ከተለያዩ ደንበኞቻቸው ከሚሰበስቡት ተቀማጭ ገንዘብ በመሆኑ፣ ይህ የደንበኞች ተቀማጭ ገንዘብ ደግሞ ወለድ የሚከፈልበት ስለሆነና አንድ አስቀማጭ ገንዘቡን በጠየቀ ጊዜ ባንኮች ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ ያለባቸው በመሆኑ የሰጡትን ብድር በወቅቱ መሰብሰብ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከዚህም ሌላ የተሰጠ ብድር ወቅቱን ጠብቆ ካልተከፈለ ገንዘቡን ለሌላ ተበዳሪ ማበደር ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ስለሚፈጥር ከብድር አመላለስ ጋር ያለው ችግር ቀላል ባለመሆኑ ባንኮች እዚህ ላይ ጠበቅ ብለው መሥራት ይኖርባቸዋል ተብሏል፡፡

የጉዳዩን አሳሳቢነት የተመለከተው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተለይ በአሁኑ ወቅት ከብድር አመላለስ ጋር ያለውን ችግር በመገንዘብ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይመለሱ የሚቆዩ ብድሮች ኢኮኖሚው ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉትን ጫና በገንዘብ ከባንኮች ጋር በመምከር እንደሚሠራበት ማሳወቁ ተገቢ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

ባንኮች በብድር መያዣነት የያዙትን ንብረት በሚሸጡበት ወቅት ግን ሕጋዊ ሒደቶችን መከተል እንደሚኖርባቸው የሚጠቁመው የባለሙያዎች አስተያየት፣ ባንኮች በመያዣት የያዙትን ንብረት ለመሸጥና ገንዘባቸውን ለማስመለስ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ይጠቅባቸው ነበር ብለዋል፡፡ ይህ አሠራር ለፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከመስጠት ጋር ተያይዞ እንዲሁም ለብድር የሚውል ገንዘብ የሕዝብ ስለሆነ በመያዣ የሚያዝን ንብረት ባንኮች የፍርድ ቤት ውሳኔ ጠብቀው መፈጸማቸው አደጋ ስላለው ተብሎ ሕጉ እንዲሻሻል መደረጉ ይታወቃል፡፡

በተሻሻለው ሕግ ባንኮች ለማስያዣት የያዙትን ንብረት በራሳቸው ውሳኔ ፍርድ ቤት ሳይሄዱ በጨረታ ለመሸጥ መብት የሚሰጣቸው በመሆኑ፣ አሁን በዚሁ መሠረት እየሠሩ ነው፡፡ አሁንም እነዚህ ባንኮች ንብረቶችን በጨረታ የሚሸጡት የራሳቸውን ህልውና ከመጠበቅ አኳያ የሚታይ መሆኑን የሚገልጹት ባለሙያዎች የጨረታ ሽያጩ ግን የተበዳሪንም መብት ባከበረ መንገድ መሆን እንደሚገባው ያመለክታሉ፡፡

በዚህ የጨረታ ክዋኔ ውስጥ ባንኮች ያበደሩትን ብድር እንዲያገኙ ተበዳሪውም ንብረቱ ተሸጦ ዕዳውን ከመለሰ በኋላ የሚተርፍ ገንዘብ ካለ የዚህ ገንዘብ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል ሕጉ ይደግፈዋል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ንብረቱ ከዋጋ በታች እንዳይሸጥበት ሕጉ የሚደግፈው መሆኑንም ያመለክታል፡፡

በጨረታ ሒደት ውስጥ አሁን አለ የተባለው ችግር ባንኮች በጨረታ ለመሸጥ የሚያወጧቸው ንብረቶችን በመጀመርያው ጨረታ ወቅት ለመሸጥ ያለመቻላቸው ሲሆን፣ በተደጋጋሚ ጨረታ ያልተሸጡ ንብረቶችን በድርድር ለመሸጥ እየተገደዱ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በቅርቡ በወጡ ጨረታዎች ላይ የገዥ ዕጦት ያጋጠመው ካለው ኢኮኖሚያዊ አቅም ጋር ተያይዞ ቢሆንም፣ ጥቂት የማይባሉ ጨረታዎች በድጋሚ እንዲወጡም እያስገደደ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በተደጋጋሚ በጨረታ ያልተሸጡ ንብረቶችን ባንኮች በድርድር ወደ መሸጥ ሊገቡም ለጨረታ አሸናፊው ብድር በማቅረብ ጭምር የሚፈጸም መሆኑም ያለውን ችግር ያሳያል ተብሏል፡፡

ባንኮች በሐራጅ የሚሸጡትን ንብረት በሁለት ተከታታይ ጨረታዎች ሊሸጡ ካልቻሉ እንዲሁም በድርድር ለመሸጥ ያደረጉት ሙከራ ካልተሳካ በአዋጅ ቁጥር 216/92 በተደነገገው መሠረት ባንኩ በንብረቱ የመነሻ ግምት ዋጋ ንብረቱን የመረከብና የራሱ ማድረግ የሚችልበት መብት አለው፡፡ ይህም በጨረታ መነሻ ዋጋው ንብረቱን ተረክበው በፈለጉበት መንገድ እንዲጠቀሙበት ዕድሉን ይሰጣቸዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/index.php/article/24908

# ሳፋሪ ኮም አገልግሎት መጀመር የሚያስችለውን ኔትዎርክ መገንባቱን አስታወቀ




ሳፋሪ ኮም የቴሌኮም አገልግሎት መጀመር የሚያስችለውን ኔትዎርክ መገንባቱን አስታወቀ።

በአዲስ አበባ የተገነባው የሳፋሪ ኮም የመጀመሪያው የመረጃ ማዕከል (ዳታ ሴንተር) የድምፅ፣ የፅሑፍ እና የኢንተርኔት ዳታ መስጠት የሚያስችል እንደሆነ የቴክኖሎጂ ኃላፊው ፔድሮ ራባሴል ተናግረዋል።

ኃላፊው በአዲስ አበባ የተገነባውን የመረጃ ማዕከል ለሀገር ውስጥ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች አስጎብኝተዋል።

የመረጃ ማዕከሉ ሙከራውን በተሳካ መንገድ እንዳከናወነም ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ 2ኛው የቴሌኮም አቅራቢ የሚሆነው ሳፋሪ ኮም ለመረጃ መዕከሉ 300 ሚሊየን ዶላር ወጭ አድርጊያለሁ ብሏል።

የቴሌኮም አገልግሎቱን ሚያዝያ ላይ እንደሚጀምር ያስታወቀው ሳፋሪ ኮም በሚቀጥለው ዓመት 25 በመቶ የኢትዮጵያ ሕዝብን ተደራሽ ለማድረግ እየሰራሁ ነው ሲልም ገልጿል።

ድርጅቱ በ10 ዓመት ውስጥ 8 ነጥብ 5 ቢሊየን ዶላር መዋለ ንዋይ ለማፍሰስ እንዳቀደም ነው ያስታወቀው።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://waltainfo.com/am/ሳፋሪ-ኮም-አገልግሎት-መጀመር-የሚያስችለ/

# አዋሽ ባንክ የሞባይል ብርና የውክልና ባንክ አገልግሎት መተግበሪያን አስተዋወቀ

አዋሽ ባንክ “አዋሽ ብር” የተሰኘ የሞባይል ብርና የውክልና ባንክ አገልግሎት መተግበሪያን ይፋ አደረገ።

የባንኩ ደንበኞች መተግበሪያውን በመጠቀም የሒሳብ እንቅስቃሴዎችን መከታተል፣ ገንዘብ ማስተላለፍ፣ ከአዋሽ ብር ወኪሎች፣ የገንዘብ መክፈያ ማሽኖች (ኤቲኤሞች) ገንዘብ ወጪ ማድረግ፣ እንደትራፊክ ቅጣትና የትምህርት ቤት ክፍያ ያሉ የተለያዩ ክፍያዎችን እና ሌሎችንም ክንውኖች መፈፀም ይችላሉ ተብሏል።

የባንኩ ሥራ አስፈፃሚ ፀሃይ ሽፈራው እንደገለፁት ዘመኑ የደረሰበትን ዲጅታል ቴክኖሎጂ በመጠቀም ባንኩ አሰራሩን እያዘመነ ይገኛል፡፡

በቀጣይም ከውጭ ባንኮች ጋር ለሚጠብቃቸው ብርቱ ፉክክር ተወዳዳሪ ለመሆን ዝግጅት እያደረጉ መሆኑን ተናግረዋል።

የሞባይል መተግበሪያው በ6 ቋንቋዎች ማለትም በእንግሊዝኛ፣ አማርኛ፣ አፋን ኦሮሞ፣ ትግርኛ፣ አፋርኛና ሶማሊኛ የሚሰራ ነው። መተግበሪያው በማንኛውም የስልክ ቀፎዎች ግልጋሎት ይሰጣል ተብሏል።

በሌላ ዜና ባንኩ በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች በ60 ሚሊዮን ብር የምግብ እህል ተገዝቶ እንዲሰጥ ቦርዱ መወሰኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ተናግረዋል።

አዋሽ ባንክ ከተመሰረተ 27 ዓመታትን አስቆጠረ ሲሆን በመላ አገሪቱ ከ680 በላይ ቅርንጫፎች አሉት።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://waltainfo.com/am/አዋሽ-ባንክ-የሞባይል-ብርና-የውክልና-ባን/

# በአኅጉራዊ የንግድ ትስስሮች ለሚቀርቡ ምርቶች የጥራት ፖሊሲ ረቂቅ ተዘጋጀ



በአገሮች መካከል ተመጋጋቢ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር በሚል ወደ ሥራ በገባው የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና አማራጭ ላይ፣ ኢትዮጵያ የምታቀርባቸው ምርቶች፣ ዓለም አቀፋዊ የጥራት ደረጃን ያረጋገጡ እንዲሆኑ የሚያስችል ብሔራዊ የጥራት ፖሊሲ ረቂቅ እያዘጋጀች እንደሆነ ተገለጸ፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ረቂቅ ፖሊሲው ከመፅደቁ በፊት የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ በረቂቅ ሰነዱ ላይ የመጨረሻ የሆነ አስተያየታቸውን የሚያቀርቡበት ዓውደ ጥናት፣ የካቲት 10 ቀን 2014 ዓ.ም. በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል አዘጋጅቷል፡፡

በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የብሔራዊ ጥራት መሠረተ ልማትና ማረጋገጥ ዘርፍ ሚኒስትር ደኤታ አቶ እንዳለው መኰንን፣ አገሪቱ ከዚህ ቀደም የጥራት ስትራቴጂ እንጂ አገራዊ ፖሊሲ አልነበራትም ብለዋል፡፡ የነበረው ስትራቴጂ ተቋማትን ሪፎርም ተሥርቶ እንዲቋቋሙ ከማድረግ የዘለለ ሚና አልነበረውም ብለው፣ በፖሊሲ ደረጃ እንዲዘጋጅ የተደረገው ሰነድ ከፍ ያለ የመንግሥት ቁርጠኝነት የታየበት ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በአገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡና ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች ላይ የጥራት ችግሮች እንዳሉ ይታወቃል ያሉት አቶ እንዳለው፣ እነዚህ ችግሮች ምላሽ የሚያገኙበት ዘዴ ቢኖር የጥራት ፖሊሲ ሰነድ ነው ብለዋል፡፡

ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና በርካታ ባለሀብቶች እንዲመጡ ጥራትን በተመለከተ የሚከናወኑ ሥራዎች ወሳኝ ናቸው ያሉት ሚኒስትር ደኤታው፣ በተለይም ከውጭ የሚመጡ ባለሀብቶች የሚጠይቁት የመጀመሪያው ጥያቄ ከጥራት መቆጣጠሪያ አኳያ ያለው ፖሊሲ ምንድነው የሚለውን ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም መንግሥት የጥራት ደረጃዎችን የሚያረጋግጥበት ፖሊሲ እንደሚያስፈልገው፣ የጥራት ፖሊሲው የሚያቋቁማቸው ተቋማት እንደሚኖሩና በተጨማሪም በቀጣይ የሚወጡ ስትራቴጂዎችም ይኖሩታል ብለዋል፡፡

በአፍሪካ ደረጃ የፓን አፍሪካ ኳሊቲ ኢንፍራስትራክቸር ፖሊሲ ተዘጋጅቷል ያሉት አቶ እንዳለው፣ በመስከረም ወር በአፍሪካ ሚኒስትሮች ደረጃ ስምምነት የተደረሰበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከሁለት ሳምንት በፊት በተከናወነው 35ኛው የአፍሪካ ኅብረት መሪዎች ጉባዔ ላይ እንደ አጀንዳ ይቀርባል ተብሎ በአጀንዳ መጣባብ ምክንያት ሳይፀድቅ መቅረቱን አስታውቀዋል፡፡

የአፍሪካ ጥራት ፖሊሲ በሚኒስትሮች ጉባዔ ስምምነት ተደርሶበት ተዘጋጅቶ እንደተጠናቀቀ የተገለጸ ሲሆን፣ በዚህም ከተካተቱት ጉዳዮች ውስጥ አገሮች በቀጣና ደረጃ የአፍሪካ የጥራት ፖሊሲ እንደሚኖራቸው፣ እንዲሁም አባል አገሮች ደግሞ የራሳቸው የጥራት ማረጋገጫ ፖሊሲ እንዲኖራቸው የሚጠይቅ ወይም የሚያስገድድ ነው ተብሏል፡፡

ኢትዮጵያ እንደ አባል አገር የራሷ የጥራት ፖሊሲ በቅርቡ እንደምታፀድቅ ተገልጾ፣ ይህም በቀጣናው ላይ ሊኖራት የሚችላትን አስተዋፅኦ ሊያሳይ በሚችል መንገድ የተቀረፀ እንደሆነ ተጠቁሟል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተብሎ ሲደራጅ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አኅጉር ነፃ የንግድና ቀጣና ላይ ምን ዓይነት ምርት ይዛ ነው መግባት የምትችለው የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ነው ያሉት አቶ እንዳለው፣ ጥራት በሌለው ምርት የተፈለገውን የገበያ መዳረሻ ማፈላለግና ማግኘት ስለማይቻል የጥራት ፖሊሲው ይህንን ለመመለስ ያስችላል ብለዋል፡፡

የፖሊሲው መዘጋጀት የኢንቨስትመንት ፍሰቱን ለማስተካከል የሚያስችል እንደሆነ የተገነገረ ሲሆን፣ በተጨማሪም የአገር ውስጥ አምራቾች ግዴታና ኃላፊነታቸው ምን እንደሆነ በግልጽ ለማስቀመጥ ፖሊሲው አስተዋጽኦ አለው፡፡ ከዚህ ቀደም የነበሩ ክፍተቶችንም ፖሊሲው የሚዘጋ እንደሆነ ያስረዱት ሚኒስትር ደኤታው፣ በቀጣይ ይህንን ለማስፈጸም የሚረዱ የማስተግበሪያ ሰነዶች፣ በተጨማሪም ለአፈጻጸም የሚረዱ ተቋማትም የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡

«በአገር ውስጥ ኢኮኖሚው በሚፈልገው ደረጃ የተደራጀ ላብራቶሪ የለንም፤» ያሉት አቶ እንዳለው፣ «ያንን ሊመልስ የሚችል እንደ አዲስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ መጠቀም የሚችል፣ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ላብራቶሪ ማቋቋም ይጠይቅ ነበር፡፡ ከሁለት ዓመት ወዲህ መንግሥት ጉዳዩን ለማስተካከል ሪፎርም ሲሠራ ነበር፡፡ ከፍተኛ ሀብት ተመድቦ የላብራቶሪና የቢሮ ግንባታዎች እየተገነባ ነው፤» ብለዋል፡፡

አቶ እንዳለው እንዳስታወቁት፣ በቀጣይ ዓለም አቀፍ ይዘትና ደረጃ ያለው የፍተሻ ላብራቶሪ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ያንን ለማድረግ ከዓለም ባንክ ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ በጀት ተመድቦ የላብራቶሪ ዕቃዎች እየተገዙ ናቸው፡፡ ብቃት ያላቸው የሰው ሀብት ባለሙያዎች የማደራጀት ሥራ እየተሠራ መሆኑን፣ መሠረተ ልማቱ ከተገነባና የሰው ኃይል ከተደራጀ፣ ጊዜው የሚጠይቀውን የላብራቶሪ ዕቃዎች አደራጅቶ ወደ ሥራ በመግባት ከሌሎች አገሮች የሚስተካከል፣ ኢኮኖሚው የሚጠይቀውን፣ የኢትዮጵያ ማምረቻ ተቋማት የሚጠይቁትን ዓይነት ምላሾችን የሚሰጥ ቁመና ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

ረቂቅ ፖሊሲው የመጨረሻውን የማጠቃለያ መድረክ ካከናወነ በኋላ ግብዓቶቹ በአጭር ጊዜ ተጠናቅረው ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ተመርቶ፣ በተያዘው ዓመት እንዲፀድቅ ጥረት እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24737

# አራት የቅመም ምርቶች እና ጓያ ዘመናዊ የግብይት ሥርዓቱን ተቀላቀሉ

ድንብላል፣ አብሽ፣ ቁንዶ በርበሬና ጥቁር አዝሙድ እንዲሁም ጓያ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የግብይት ስርዓታቸው በይፋ መጀመሩን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት አስታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት እንደገለጸው እነዚህ ምርቶች ሲካተቱ ምርት ገበያው የሚያገበያያቸው ምርቶች ብዛት ከ12 ወደ 17 ከፍ ያደርገዋል ተብሏል፡፡

አንድ ኩንታል ጥቁር አዝሙድ በ26 ሺህ 500 ብር፥ አንድ ኩንታል አብሽ በ12 ሺህ ብር መገበያየቱም ተጠቁሟል፡፡

በየዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከ348 ሺህ ቶን በላይ ቅመማ ቅመም ይመረታል ነው የተባለው፡፡

እነዚህ ቅመማ ቅመሞች በአብዛኛው በዓለም ገበያ ተፈላጊ ሲሆኑ፥ በተለይም አብሽን በማምረት ኢትዮጵያ ከፍተኛውን ድርሻ ትወስዳለች።

በየዓመቱ ወደ ውጭ የሚላከው የቅመማ ቅመም ምርት 15 ሺህ ቶን ሲሆን ፥ ከጠቅላላው ዓመታዊ ምርት መጠን ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆኑ ተገልጿል።



ጓያም በየዓመቱ ከ2 ነጥብ 6 ሚሊየን ኩንታል በላይ እየተመረተ ወደ ውጭ የሚላከው ከ775 ሺህ ኩንታል ያልዘለለ መሆኑን ከምርት ገበያ ድርጅቱ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/አራት-የቅመማ-ቅመም-ምርቶች-እና-ጓያ-ዘመና/◦

# በአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጣና ተወዳዳሪ ለመሆን የአነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም በእጥፍ ማሳደግ እንደሚገባ ተገለጸ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ተወዳዳሪና ተጠቃሚ ለመሆን፣ በአገር ውስጥ ያሉ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎችን አቅም በእጥፍ ማሳደግ እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

የነፃ የንግድ ቀጣናው በአፍሪካ አገሮች መካከል ተመጋጋቢ የሆነ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ያስችላል የተባለለት የንግድ ሥርዓት ሲሆን፣ ኢትዮጵያ የአምራች ኢንዱስትሪዎችንና ሥራ ፈጣሪዎችን ሊያበረታታ የሚችል ተግባር ከወዲሁ መሥራት እንዳለበት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የንግድና ልማት ኮንፈረንስ (UNCTAD) በአፍሪካ የልዩ ፕሮግራም ዳይሬክተር ፖል አኪውሚ ተናግረዋል፡፡

አምራች ኢንዱስትሪዎች የመሥሪያ ካፒታልና የዳበረ አቅም ካልተፈጠረላቸው በቀጣናው ተወዳዳሪ የመሆን ዕድላቸው የላላ እንደሚሆን የተገለጸው፣ የተመድ የንግድና ልማት ኮንፈረንስ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመሆን የካቲት 24 እና 25 ቀን 2014 ዓ.ም. በአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅምና መዋቅራዊ ግንባታ ላይ ውይይት በተካሄደበት ወቅት ነበር፡፡

በርካታ አገሮች ፈርመውበት ወደ ሥራ እየገባ ባለው ነፃ የንግድ አሠራር ውስጥ በኢትዮጵያ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎች፣ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ የሆኑና በመሣሪያ የተደራጁ፣ እንዲሁም የንግድ ሥርዓትን ሊያጠናክሩና ሕግን ሊያከብሩ የሚችሉ ተቋማት መፈጠር እንዳለባቸው ዳይሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

ለውይይቱ የቀረበ ሰነድ እንደሚያመለክተው ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ያላት የንግድ ድርሻ አንድ በመቶ አይሞላም፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ደኤታ አቶ ታረቀኝ ቡልልታ እንደገለጹት፣ አምራች ኢንዱስትሪው እ.ኤ.አ. በ2030 የአገሪቱን 15 በመቶ የሥራ ዕድል የሚፈጥር ዘርፍ በማድረግ ወደ የአምስት ሚሊዮን ዜጎችን የሚይዝ የሥራ ዘርፍ ይሆናል፡፡ አሁን ከ45 በመቶ ያላለፈውን የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ወደ 85 በመቶ በማሳደግ፣ ለአገሪቱ እያበረከተ ያለውን አራት ሚሊዮን ዶላር ወደ ዘጠኝ ቢሊዮን ዶላር ያሳድገዋል ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል በቅርቡ ከሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ጋር በተገናኘ ከዓመታት በፊት በአሜሪካ መንግሥት ለኢትዮጵያ ተሰጥቶ የነበረው የአጎዋ ከቀረጥ ነፃ የንግድ ዕድል መነሳት ምንም እንኳ ሴቶችና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ሕይታቸውን ይመሩበት የነበሩ ዜጎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚጎዳ ቢሆንም፣ መንግሥት ሸቀጦችን በቻይና መንግሥት በተፈጠረ የዜሮ ታሪፍ የንግድ ዕድል፣ እንዲሁም የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጣና ዕድልን በመጠቀም ገበያውን ለማካካስ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍፁም አሰፋ (ዶ/ር) ናቸው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24867

# ሦስት የውጭ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ የብረት ፋብሪካ ለመገንባት ከመንግሥት ጋር እየተደራደሩ ነው

በኢትዮጵያ የብረታ ብረት ማምረቻ ፋብሪካዎቻቸውን ለመትከል የጠየቁ ሦስት ግዙፍ የውጭ ኩባንያዎች ከመንግሥት ጋር እየተደራደሩ መሆኑ ታወቀ።

ኩባንያዎቹ በብረታ ብረት ዘርፍ በዓለም ላይ የሚታወቁ ግዙፍ ኩባንያዎች መሆናቸውን የሪፖርተር ምንጮች ገልጸዋል።

ጥያቄ ያቀረቡት የጣሊያን፣ የቱርክና የኮሪያ ኩባንያዎች መሆናቸውን የገለጹት ምንጮቹ፣ ፋብሪካዎቻቸውን በኢትዮጵያ ለመትከል ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር እየተደራደሩ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

ኩባንያዎቹን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን የገለጹት ምንጮቹ፣ መንግሥት ፍላጎቱን ለማሳካት በአዲስ አበባ ከሚገኙ ኩባንያዎቹን ከሚወክሉ ኤምባሲዎች ጋር ጭምር ንግግር ማድረጉን ገልጸዋል።

በተለይም በኢትዮጵያ የብረት ብረት ፋብሪካውን ለመትከል ጥያቄ ያቀረበው የጣሊያኑ ኩባንያ ከመንግሥት ጋር የሚያደርገውን ወይይት በተሳካ ሁኔታ ከፈጸመ፣ በአገር ውስጥ የሚታየውን የብረታ ብረት ምርት አቅርቦት ትርጉም ባለው መልኩ እንደሚፈታ ምንጮቹ ገልጸዋል።

የጣሊያኑ ኩባንያ ዳንኤሌ ኤስፒኤ የሚባል ሲሆን፣ በዓለም ላይ ግዙፍ የብረት ማቅለጫና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ያለው ስመጥር ኩባንያ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ በዘርፉ ልምድ ያካበተ እንደሆነም ተገልጿል።

የብረታ ብረት ፋብሪካዎችን ገንብቶ በማስረከብም የተዋጣለት እንደሆነና ከዘጠና በላይ መሰል ፋብሪካዎችን በተለያዩ አገሮች እንደተከለም ገልጸዋል።

የካቲት 14 ቀን 2014 ዓ.ም. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝተው ማብራሪያ የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ፣ ከውጭ የሚገቡ የፕሮጀክት ምርቶች ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ መናር በአገሪቱ ለሚስተዋለው የዋጋ ግሽበት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የብረት ምርት ዋጋ 65 በመቶ መጨመሩን ገልጸው፣ የብረት ምርትን በአገር ውስጥ መተካት ካልተቻለ አስቸጋሪ እንደሚሆን አስረድተዋል።

በመሆኑም የብረት ምርትን በአገር ወስጥ ለማምረት መንግሥት ሰፊ ጥረት መጀመሩን ገልጸው፣ የተጀመረው ጥረት የብረት ምርትን በተወሰነ ደረጃ ከውጭ ማስገባት ለመቀነስ ያስችላል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/24823

# ብሔራዊ ባንክ የመመሥረቻ ካፒታል ያላሟሉ ባንኮች የጠየቁትን የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ውድቅ አደረገ

በምሥረታ ላይ የነበሩ ባንኮች የተጠየቀውን የመመሥረቻ ካፒታል ባለማሟላታቸው ጊዜ እንዲጨመርላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ውድቅ አደረገ።

ብሔራዊ ባንክ በመጋቢት ወር 2013 ዓ.ም. ባወጣው መመርያ፣ ባንክ ለማቋቋም ይጠይቅ የነበረውን የተከፈለ ካፒታል መጠን ወደ አምስት ቢሊዮን ብር ማሳደጉን ማስታወቁ ይታወሳል፡፡

በመመርያው መሠረት ነባር ባንኮች በአምስት ዓመታት ውስጥ ካፒታላቸውን አምስት ቢሊዮን ብር እንዲያደርሱ፣ አዲስ የሚመሠረቱ ባንኮች ደግሞ በመመርያው የተደነገገውን ለማሟላት እስከ ሰባት ዓመት የጊዜ ገደብ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በመመርያው በምሥረታ ላይ ያሉ ባንኮች 500 ሚሊዮን ብር ካፒታል በማሟላት ለመቋቋም የስድስት ወራት ጊዜ ተሰጥቷቸው ነበር። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠየቀውን የተከፈለ ካፒታል አሟልተው ባንኩን መመሥረት ካልቻሉ ግን፣ በአዲሱ መመርያ መሠረት ባንክ ማቋቋም የሚችሉት የተከፈለ ካፒታላቸው አምስት ቢሊዮን ብር ሲደርስ መሆኑም ተደንግጓል።

በተሰጠው ጊዜ ውስጥም በምሥረታ ላይ የሚገኙ ባንኮች የተጠየቀውን ካፒታል አሟልተው ለመቋቋም አስቸጋሪ መሆኑን በመጥቀስ ለብሔራዊ ባንክ የጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፣ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱን የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ሰሎሞን ደስታ ለሪፖርተር ገልጸዋል።

የተሰጠው የጊዜ ገደብ በማነሱ ሳይሆን ባንኮቹ ካፒታሉን የማሟላት አቅም ይዘው ምሥረታ ውስጥ ባለመግባታቸው በመሆኑ፣ የጊዜ ማራዘሚያው አስፈላጊ ሆኖ አለመገኘቱን አክለዋል።

በ2013 ዓ.ም. በምሥረታ ላይ ከነበሩት 17 ባንኮች ውስጥ የተጠየቀውን የመመሥረቻ ካፒታል ያላሟሉት 13 እንደሆኑ አቶ ሰሎሞን ተናግረዋል።

በምሥረታ ላይ ከሚገኙት አንዱ ግዕዝ ባንክ በአሁኑ ወቅት 300 ሚሊዮን ብር የተከፈለ ካፒታል ሲኖረው፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጠየቀውን ካፒታል ባለማሟላቱ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ብሔራዊ ባንክን ቢጠይቅም ተቀባይነት አለማግኘቱን የባንኩ አደራጅ አቶ ላይን ክንፈ ገልጸዋል።

ሆኖም የመመሥረቻ ካፒታሉን ለማሟላት የተሰጠው ጊዜ በጣም ጠባብ መሆኑን፣ የአክሲዮን ሽያጩ የሚደረገው በገበያው ላይ ካሉት ባንኮች ጋር በሚደረግ ውድድር የሚካሄድ ስለሆነ ፈታኝ እንዳደረገው አክለዋል።

በሰባት ዓመታት እንዲሟላ የሚጠበቀው አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ረዥም ዕድሜ ላስቆጠሩት ባንኮች ከተሰጠው የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ መሆኑን ተናግረዋል። በቀጣይ ግዕዝ ባንክ ከሌሎች ጋር ተዋህዶ ይቀጥል ወይስ ራሱን ችሎ የሚፈለገውን ካፒታል ያሟላ የሚለውን ለመወሰን፣ አደራጅ ኮሚቴው በምክክር ላይ መሆኑን አቶ ላይን ጨምረው ገልጸዋል።

ሌላው በምሥረታ ላይ የሚገኘው ዳሞት ባንክ የተጠየቀውን የመመሥረቻ ካፒታል ማሟላት አለመቻሉን ገልጿል። የባንኩ አደራጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ኤሊያስ ሎሃ እስካሁን ምን ያህል የተከፈለ ካፒታል መሰብሰቡን ማወቅ እንዳልተቻለ ገልጸው፣ በኦዲት ሒደት ላይ እንደሆነ ተናግረዋል።

በሰባት ዓመት ውስጥ እንዲሟላ የተጠየቀውን ሰባት ቢሊዮን ብር መመሥረቻ ካፒታል ማሟላት የማይቻል በመሆኑ፣ የባንኩን ምሥረታ በማቋረጥ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለባለአክሲዮኖች ሊመልስ መሆኑን ተናግረዋል።

አዲስ ለሚመሠረቱ ባንኮች የተሰጠው የካፒታል ማሟያ ጊዜን በተመለከተ ለሪፖርተር አስተያየታቸውን ያጋሩት በባንክ ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት በመሥራት ላይ የሚገኙት አቶ እሸቱ ፋንታዬ፣ የሚመሠረቱት ባንኮች የሚጠበቅባቸውን ማሟላት ያልቻሉት በራሳቸው ድክመት እንጂ ጊዜው በማነሱ ወይም ገንዘቡ በመብዛቱ አይደለም ይላሉ።

ይልቁንም የሚመሠረቱበትን ዓላማ በውል አለመለየትና የአደራጆች ጠንካራ አለመሆን ትልቁ ችግር መሆኑን ገልጸዋል። በ2013 ዓ.ም. በምሥረታ ላይ ከነበሩ ባንኮች ውስጥ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተጠየቀውን አሟልተው የተመሠረቱ ባንኮች መኖራቸውን በማሳያነት በመጥቀስ፣ ሌሎቹም ጥሩ አስተዳደር ቢኖራቸው ካፒታሉን ማሟላት ከባድ አይሆንባቸውም ነበር ብለዋል።

በባንክ ዘርፍ ከፍተኛ የገበያ ዕድል መኖሩን የጠቀሱት አቶ እሸቱ፣ ይህንን ክፍተት ከመመልከት ይልቅ የሚደራጁት በትውውቅና ተገቢ ባልሆኑ ሁኔታዎች በመሆኑ ውጤታማ መሆን ሳይችሉ እንደሚቀሩ አብራርተዋል።

በሰባት ዓመት ውስጥ እንዲሟላ የተጠየቀው አምስት ቢሊዮን ብር ካፒታልም ቢሆን ሊደረስበት የሚችል መሆኑን አስረድተዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24743

# የገልፍ የምግብ ኤክስፖ ኢትዮጵያ የውጪ ምርቶቿን እንድታስተዋውቅ እድል ፈጥሯል



ኢትዮጵያ በዱባይ ገልፍ የምግብ ኤክስፖ መሳተፏ የውጪ ምርቶቿን እንድታስተዋውቅ እድል መፍጠሩን የውጭ ንግድ እና ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ ዳንጌ ቦሩ ገለፁ፡፡

በዱባይ ወርልድ ትሬድ ሴንተር በተካሄደዉ ገልፍ ፉድ ኤክስፖ ኢትዮጵያ የተለያዩ የምግብ ምርቶችን አቅርባለች፡፡

በኤክስፖው ላይ የተገኙት በንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የውጭ ንግድ እና ፕሮሞሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ዳንጌ ቦሩ እንደተናገሩት፥ ኢትዮጵያ በርካታ አለም ዓቀፋዊ ድርጅቶች በአንድ ጣራ ስር በተገኙበት የምግብ ኤክስፖ ላይ መሳተፏ ሀገሪቱ ያሏትን የወጪ ምርቶች ለማስተዋወቅ አድል ፈጥሯል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በጥራጥሬ እና ቅባት እህሎች፣ በቡና እና በቅመማ ቅመም፣ በማር እና በስጋ እንዲሁም በቁም እንስሳት ምርቶች ከፍተኛ አቅም አላት ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፥ የዱባዩ የምግብ ኤክስፖ በዘርፉ ላይ ከሚሰሩ አለም አቀፍ ኩባንያዎች ጋር ተቀራርቦ ለመስራት አድል የፈጠረ መሆኑንም ገልፀዋል፡፡

በእለቱም በተለያዩ የወጪ ምርቶች ላይ ከኢትዮጵያ ጋር የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት አብሮ ለመስራት ስምምነት ማድረጋቸውን ሚኒስትር ዴኤታዉ ተናግረዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/የገልፍ-የምግብ-ኤክስፖ-ኢትዮጵያ-የውጪ-ም/

# የድንጋይ ከሰል ለማምረት ፈቃድ ለወሰዱ ድርጅቶች አስቸኳይ የውጭ ምንዛሪ እንዲቀርብ ተወሰነ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በታኅሳስ ወር ባሳለፈው ውሳኔ የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ ለማምረት ፈቃድ ለወሰዱ ስምንት ድርጅቶች፣ አስቸኳይ የውጭ ምንዛሪ እንዲቀርብ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወሰነ።

በውሳኔው መሠረትም ብሔራዊ ባንክ የካቲት 7 ቀን 2014 ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደብዳቤ መጻፉን የሪፖርተር ምንጮች ገልጸዋል።

እንደ ምንጮቹ ገለጻ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የድንጋይ ከሰል የማምረት ፈቃድ ለተሰጣቸው ስምንት ድርጅቶች፣ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ማሽን ግዥ የሚውል የውጭ ምንዛሪ «የቅድሚያ ቅድሚያ» ሰጥቶ እንዲያስተናግዳቸው ታዟል።

በመሆኑም የድንጋይ ከሰል የማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው ስምንት ድርጅቶች አስፈላጊውን የባንክ ፎርማሊቲ አሟልተው ሲመጡ፣ «የቅድሚያ ቅድሚያ» እንዲሰጣቸው መታዘዙን ምንጮቹ ገልጸዋል።

ለስምንቱ ድርጅቶች በአስቸኳይ እንዲቀርብ የተፈቀደው አጠቃላይ የውጭ ምንዛሪ መጠንም 25.4 ሚሊዮን ዶላር እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

ብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን፣ ኤልኔት ቴክኖሎጂና ኢስት አፍሪካ ማዕድን ኮርፖሬሽን፣ ሰን ማይኒንግ ኤንድ ትሬዲንግ ኩባንያ እያንዳንዳቸው 4.1 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ እንዲሰጣቸው፣ በብሔራዊ ባንክ ደብዳቤ ላይ እንደተጠቀሰ፣ ይህ መጠንም ለስምንቱ ኩባንያዎች በተናጠል ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ ትልቁ እንደሆነ ምንጮች አስረድተዋል።

የድንጋይ ከሰል የማምረት ፈቃድ የወሰዱት ስምንቱ ኩባንያዎች አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ካፒቴል ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ መሆኑን፣ በዓመት በአማካይ 4.2 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል የማምረት አቅም እንዳላቸው መዘገባችን ይታወሳል።

ስምንቱ ኩባንያዎች በቀጣዮቹ አሥር ዓመታት ውስጥ ያመርታሉ ተብሎ ከሚጠበቀው የድንጋይ ከሰል ምርት 98 ቢሊዮን ብር የሽያጭ ገቢ ያገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል።

መንግሥት በእያንዳንዱ የድንጋይ ከሰል ፕሮጀክት ውስጥ የአምስት በመቶ ነፃ ድርሻ የያዘ ሲሆን፣ ፕሮጀክቶቹ የሚከናወኑባቸው ክልሎች ደግሞ ሁለት በመቶ የነፃ ድርሻ ይኖራቸዋል።

የድንጋይ ከሰልን ለኃይል ምንጭነት ለሚጠቀሙ ፋብሪካዎች በተለይም የሲምንቶ ፋብሪካዎች ያለባቸውን የድንጋይ ከሰል አቅርቦት ችግር ለመፍታት፣ መንግሥት በየዓመቱ 270 ሚሊዮን ዶላር ወጪ በማድረግ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ሲያስገባ መቆየቱ ይታወቃል።

የድንጋይ ከሰል በአገር ውስጥ እንዲያመርቱ ፈቃድ የተሰጣቸው ስምንት ድርጅቶች፣ ከውጭ የሚገባውን ምርት በአገር ውስጥ የመተካት ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል።

በዚህም ምክንያት መንግሥት የድንጋይ ከሰልን ከውጭ እንዳይገባ ክልከላ መጣሉን፣ ከማዕድን ሚንስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ኩባንያዎቹ በአንድ ዓመት ውስጥ፣ የአገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን በማምረት እንደሚያቀርቡ ይጠበቃል።

ከጥቂት ሳምንታት በፊት አስተያየታቸውን ለሪፖርተር የሰጡት የማዕድን ሚኒስትሩ ታከለ ኡማ (ኢንጂነር)፣ «የእነዚህ ፋብሪካዎች ግንባታ አገራችንን በየዓመቱ የምታወጣውን የመቶ ሚሊዮን ዶላሮች ወጪ የሚያድን ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች ግብዓት የሆነውን የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን በሟሟላት የሲሚንቶ ምርትን የሚያሳድግ ይሆናል፤» ማለታቸው ይታወሳል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/24811

ዋና አዘጋጅ፡-

ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡-

ዮሴፍ ተሾመ

አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

Facebook: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Twitter: https://twitter.com/EthiopiaChamber

Telegram: t.me/ethiopiachamber

## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

Mexico Square, ECCSA Building

Ground Office , Room No. 13/14

Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm

Tel: 251-115514005

Mob. 0966038499

Fax: 251-115517699

# የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ

ወይም

በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ማዕከል**